# ሙያውን አዋርዶ ለማትረፍ መሯሯጥ!!

ዲበኩሉ 1/1/14

የፕሬስ ነጻነት እንደ ሌሎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሁሉ የአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማትን ጨምሮ በዴሞክራሲያዊ ሃገራት ሕጎች ውስጥ ተቀባይነት ያለው የዜጎች/የሰዎች ዴሞክራሲያዊ መብት ነው፡፡ የፕሬስ ነጻነት ሃሳብን በጽሁፍና ሌሎች የሥነጥበብ ውጤቶች በነጻነት የመግለጽ መብት ነው። ለጋዜጠኞች ብቻ የተፈቀደ ልዩ መብትም አይደለም፣ የሁሉም ዜጎች መብት እንጂ፡፡ የፕሬስ ነጻነት የግልና የመንግስት ጋዜጠኞችና ሚዲያ የሚል የልዩነት ወይም አድሎአዊ መስመር ያሰመረና አይደለም፡፡ በሃገራችን የፕሬስ ነጻነት ተገቢውን እውቅና ወይም ሕገመንግሥታዊ ዋስትና አግኝቶ በታሪካችን ተግባራዊ መሆን የጀመረው ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ነው፡፡

ይህ የላቀ ዴሞክራሲያዊ መብት ወደ ተግባር ሲለወጥ ሚዛናዊና ተጨባጭ አድሎአዊነት የሌለው መሆን አለበት፡፡ የፕሬስ ነጻነት ሳንሱር ሳይደረግበትና ጫና ሳይኖረው በነጻነትና በሰላማዊ መንገድ ሃሳብን የመግለጽና አመለካከትን የማራመድ መብት ቢሆንም የሌላውን ግለሰብም ሆነ ቡድን መብት ወይንም ሀይማኖት፣ እምነትና አመለካከት እንዲድጥ፤ ማንነቱን፣ ክብሩንና ባህሉን እንዲያንቋሽሽ ወይም ለሽብር ተግባር፣ለግጭትና ሁከት መቀስቀሻነት እንዲውል የየትኛውም አገር ሕግ አይፈቅድም፡፡

የፕሬስ ነጻነት፤ ስሙን በመጠቀም ትርፍ ለመሳብ ብቻ ሲባል ከሙያው ሥነ ምግባር ባፈነገጠ መልኩ ጥላቻን ለማስረጽ የሚጠቀሙበት መብት አይደለም፡፡ የፕሬስ ነጻነት የመረጃ ምንጮችን ተአማኒነት፤ የሁለት ወገኖችንና የገለልተኛ ወገኖችን የተለያዩ ሃሳቦችና አመለካከቶች በእኩል ድርሻ የማንሸራሸር ሃላፊነትን ተግባራዊ ያደርጋል እንጂ አንድ ጥግ ይዞ በአንድ ወገን ላይ ብቻ የሚረባረብ፤ ጥላቻን የሚያመርትና የሚያዛምት አይደለም፡፡ ሀሰትን እውነት አድርጎ ማቅረብ፣ ለአንድ ወገን ተገዝቶ በሌላው ወገን ላይ መዝመት፤ መሰረታዊ የሀሳብና የአስተሳሰብ ልዩነቶች መከበር አለባቸው የሚለውን የዲሞክራሲ መሰረታዊ መርህ በመግደል የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ መሆን የለበትም፡፡

የግለሰቦችን ስም ማጥፋት፤ ማጥላላት፤ ስብዕናቸውንና ክብራቸውን ማጉደፍ ተአማኒነት የሌለው የፈጠራና የሀሰት ወሬ ማሰራጨት የፕሬስ ነጻነት ማለት አይደለም፡፡ አብሮነትን የሚያደፈርስ፤ ሕዝቡን ለሁከትና ለብጥብጥ ለትርምስ እንዲነሳ ከጀርባ የፋይናንስ ድጋፍ

በሚያደርጉላቸው ሀይሎች እየተረዱ የሚዘወሩ መሆን የለባቸውም። ለሕዝብ የተሳሳተ መረጃን በማቅረብ እምነት እንዲያጣና ጥላቻ እንዲያደርበት በተሰላ መንገድ መቀስቀስ የፕሬስ ነጻነት ዓላማም ግብም አይደለም፡፡ የፕሬስ ነጻነት መብት የህዝቦች ሙሉ መብት እንጂ ለጥቂቶች ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ልዩ መብትም አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም፡፡

የሕዝብን መብት ሰላምና ጸጥታ፤ እለታዊ ሕይወቱንና ኑሮውን፤ ማህበራዊ መስተጋብሩን የሚያናጉና የሚያደፈርሱ ጽሁፎችን እያተሙ ሃላፊነት በጎደለው መልኩ ማሰራጨት በዚህም የገበያ ትርፍ መሰብሰብ፣አልፎ ተርፎም ለሌሎች ስውር ፖለቲካዊ አጀንዳ ሽፋን ሰጭ፣ተላላኪና አገልጋይ ሁኖ መስራት የፕሬስ ነጻነት መርህ አለመሆኑን የዘነጉ አንዳንድ ፕሬሶች በሃገራችን ማቆጥቆጥ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በእርግጥ ይህ ትክክለኛው መንገድ ባለመሆኑ ጥቂት የማይባሉ የግል ፕሬሶች በራሳቸው ምክንያትና ግዜ ዳር ሳይደርሱ ከመንገድ ቀርተዋል፣ አንዳንዶች ደግሞ ሙሉ ለሙሉ አለያም ቢያንስ ከሞላ ጎደል ሕግና ሥርዓቱን ጠብቀው በመንቀሳቀሳቸው እስካሁንም ቀጥለዋል። ሌሎችም በፊት ለፊት በር ወጥተው በጓሮ በር በመግባት "በአዲስ መልክ ሥራ ጀምረናል" የሚሉትን ወይም አንድ ባልንጀራዬ ብዙ ጊዜ "ፍራሽ አዳሾች" አንዳንድ ጊዜም አዘጋጆቹን አስመሳይ ጋዜጠኞች/PSEUDO-JOURNALISTS/ እያለ ሁሌም የሚጠራቸውንም እያሰብን በእርግጥም በርካታ አዳዲስ የግል ፕሬሶች በየጊዜው የሚዲያ ኢንዱስትሪውን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ የፕሬስ ነጻነት ትሩፋት በመሆኑ በትክክለኛው የሙያ ጎዳና እየተጓዙ ላሉት እሰዬው የሚያስብል ነውና ሊበረታታ ይገባዋል። በበኩሌም የግል ፕሬሱ ይበልጥ እንዲያብብና እንዲጠናከር መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል እላለሁ።

ሁኔታው ይህ ይሁን እንጂ በውስጥና በይበልጥም በውጭ ባሉ ተቃዋሚ ሀይሎች/ጽንፈኞች የፋይናንስና የሞራል ድጋፍ እየተደጎሙ የእነሱ መሳሪያ በመሆን ለረዥም ጊዜ ሲያገለግሉ የነበሩ፤ በዚህም በርካሽ ጥቅም ራሳቸውን ያቃለሉና ያዋረዱ ምናልባትም በጣም ጥቂቶቹ በአጭር ጊዜ ሕይዎታቸውን የቀየሩ፣ ሆኖም በፕሬስ ነጻነት ስም ሲነግዱ የነበሩና ዛሬም ያሉ ግለሰቦችን መታዘባችን አልቀረም። መሰረታዊ ዓላማቸው፤የፈጠራ ወሬ ነግዶ ማትረፍ እንጂ ለህዝብና ለሃገር ጥቅም ወይም ብሔራዊ ክብር መቆርቆር አልነበረም፣አይደለምም፡፡ ምንጊዜም ፍላጎታቸው ሕዝብንና ሃገርን ለችግር ዳርጎ በሕዝብ ሰቆቃ ማትረፍ፤ገንዘብ ማግበስበስ ሆኖ ሳለ "ለሕዝብና ለሀገር እንቆረቆራለን፤ መስዋእትነት የምንከፍለው ለሀገርና ለሕዝብ ነው" ሲሉ መስማት ንጹህ ሕሊናን እያቆሰለ የምሬት ሳቅ ያስቃል፣አዕምሮን

ያደማል፡፡ ዳሩ ግን ሕሊናቸው እውነቱን ስለሚያውቀው በዚህ ስራቸው ሊያፍሩ እንጂ ሊመጻደቁና ሊኩራሩ ባልተገባቸው ነበር፡፡

በፕሬስ ነጻነት ስም በሚነግዱ ኃይሎች ስውር ተንኮል ተጠልፎ ነገር ግን ለሙያው ክብርና ነጻነት የሚሰራ መስሎት የሚታየው ጋዜጠኛ ካለ አንድ አፍታ ቆም ብሎ ራሱን በመጠየቅ ከሕሊናው መታረቅ ይገባዋል፡፡ በእርግጥ ለነማን ነው የምሰራው? ከጀርባ ማን ምን እያደረገ ነው? ብሎ መጠየቅ ግድ ይለዋል፡፡ ከትላንቶቹ ውድቀት መማርም ተገቢ ነው፡፡ በያዙኝ ልቀቁኝ ድንፋታና ኃላፊነትና ሙያዊ ሥነ ምግባር በጎደለው አካሄድ አንዳንድ የግል ፕሬሶች ከሕትመት ውጭ መሆን ከራሳቸው ሁኔታ ጋር በተያያዘ ምክንያትና አንዳንዶችም ከአቅም ማጣት እንጂ በፕሬስ አፈና ምክንያት ተዘግተዋል የሚለው የፈጠራ ውንጀላ ፈጽሞ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሃገሪቱ ሕገመንግሥት ለዜጎች ያጎናጸፈውን መብት ተጠቅሞና ሕግን ተከትሎ በሰላማዊ መንገድ የሚሰራን ፕሬስ ወይም ጋዜጠኛን መብት የትኛውም የመንግሥት አካል ሊጋፋ ወይም ይህን ሕገመንግሥታዊ መብቱን ሊነሳ የሚያስችለው ሕጋዊ መሰረት የለውና። ይህ ተፈጽሞ ቢገኝ እንኳ ማንም ዜጋ ቢሆን መብቱን በፍርድ ቤት ማስከበር የሚችልበት ሙሉ ነጻነት እንዳለው ይታወቃል።

በፕሬስ ነጻነት ስም የጽንፈኞች የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ መድረክ የሆኑ አንዳንድ የግል ፕሬሶች ከስፖንሰሮቻቸው በተመደበላቸው ገንዘብ እንደሚንቀሳቀሱና በእነዚህ ኃይሎች ተጽዕኖ ሥር መውደቃቸው ይታወቃል። በግል ጋዜጠኝነት ካባ ተሸፍነው አሜሪካና አውሮፓ ላሉ የጽንፈኛ ተቃዋሚ ሚዲያዎች የሚሰሩ ወገኖች ስለመኖራቸው ከጥርጣሬም በላይ ነው።

ይህ በሁለት ካባ /በሕጋዊና በሕገወጥ/ ተሸፍኖ የሚሰራው ሀይል ነው እንዳሻው እየጻፈም እየዘለፈም፣ እየተቸም፣ እየተሳደበም፣ ኪሱን በመሙላት የፕሬስ ነጻነት የለም ሲል የሚደመጠው፡፡ የፕሬስ ነጻነት ባይኖር ኖሮ ይህ ሁሉ የግል ጋዜጣና መጽሄት ለአደባባይ አይበቃም ነበር፡፡ ሊታረምና ሊስተካከል የሚገባው ችግር አለ ቢባል እንኳ በተጨባጭ ምክንያትና በሃቀኝነት ላይ ተመስረቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማቅረብ፣ መንግሥትን መተቸት፣ገንቢ አስተያዬቶችንና መፍትሔዎችን ማመላከት አንድ ነገር ነው፡ ፡ ጭርሱንም የፕሬስ ነጻነት የለም ብሎ መደምደም ግን ጭፍን ክህደት ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ያለውን ነጻነት ተጠቅሞ የራስን ብቃትና እውቀት እያሳደጉ መሄድ ጠቃሚ ነው። በተለይም መንግሥትን በተለያየ መልኩ በግልጽ የሚተቹ አስተያዬቶችና

አመለካከቶች ያለገደብ በነጻነት እየተስተናገዱ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ከሁለት አሰርት ዓመታት በፊት ሊሰማ ይችል የነበረና "ኧረ የፕሬስ ነጻነት ያለህ!" የሚያስብል፣ በባዶ ሜዳ ሙሾ የሚያስወርድ ነገር አሁን ምን አመጣው? ብሎ መጠየቅ ተገቢነት ያለው ይመስለኛል፡፡

እጅግ አስገራሚው ነጥብ ቀድሞ ከነበረው የተዛባ አስተሳሰብና አመለካከት በመነሳት ወይንም ስለፕሬስ ነጻነት በቂና ተገቢ የሆነ ግንዛቤና እውቀት ካለመጨበጥም የተነሳ አብዛኛው የግሉ ፕሬስ የፕሬስ ነጻነት መብት የእሱና የእነርሱ የጥቂት ጋዜጦች መጽሄቶችና የግል ጋዜጠኞች ልዩና ብቸኛ መብት አድርጎ ይወስደዋል፣ ይህ አደገኛ ስህተት ነው፡፡

ማነው የፕሬስ ነጻነትን የግሉ ፕሬስ ብቸኛ መብት ያደረገው? የፕሬስ ነጻነት የዜጎች ሁሉ መብት ነው፡፡ በእርግጥ ከሙያው አንጻር በሕትመት ሚዲያው ዘርፍ ያሉ ጋዜጠኞች ብዙ ስለሚጽፉና ስለሚዘግቡ ሕግን ተላልፎ ከመገኘት የተነሳ ከሚያስከትለው ሕጋዊ ተጠያቂነት አንጻር ሊጠየቁ ስለሚችሉ የጻፍነው የፕሬስ ነጻነት መብታችንን ተጠቅመን ነው የሚለው የመከላከያ ምላሽ ሊሰማ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን የግሉም ሆነ የመንግስት ጋዜጠኛው ከሙያ ስነ ምግባሩም ሆነ በብሄራዊና ዓለም አቀፋዊ የፕሬስ ነጻነት መርሆዎችና ሕጎች ላይ በግልጽ ከሰፈረው ውጭ ተራምዶ ቢሄድና ይህ ደግሞ የተለያዩ ችግሮችን በሕዝብና በሀገር ላይ የሚያመጣ ሆኖ ሲገኝ በሕግ አይጠየቅም፤ አይዳኝም፤ ማለት አይደለም፡፡ እንዳሻው በልቅነትና በሕገ ወጥነት፤ በስርአት አልበኛነት ሊፈነጭ ይችላል የሚል ሕግ የለም፡፡ ይህንን አይነት ሁኔታ የፕሬስ ነጻነት አሰፈንን የሚሉት እንግሊዝና አሜሪካንም በሕግ ከመዳኘት አላለፉም፡፤ እንዲያውም እንግሊዝ አዲስ ሕግ በፓርላማ እንዲያወጣ እስከማድረግ ተረማምዳለች፡፡

ጽንፈኛና አክራሪ ፖለቲከኞች የሚጠቀሙበት አንዱ መንገድ ጋዜጦች ባሻቸው መንገድ ሕግ ተላልፈው እንዲጽፉ መገፋፋትና ጋዜጠኛው በህግ ተጠያቂ ሲሆን ያንን በዓለም አቀፍ ድርጅቶች በማስተጋባት በአገር ላይ ጫናዎችን ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት ነው፣ ይህም የተቀናጀና የተጠና ሴራ ውጤት ነው፡፡ የፕሬስ ነጻነትን በመጠቀም የተለያዩ ጥቅሞቻቸውንና የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ የውጭ ሀይሎች በመሳሪያነት የሚጠቀሙት በዋናነት በሀገር ውስጥ ያለውን የግል ሚዲያ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተደጋጋሚ በአፍሪካም ሆነ በእኛው ሀገር ውስጥ ታይቷል፡፡ ይህ ግን የት ድረስ ሊያዛልቅ እንደሚችል እንዳለፉት ጊዚያት ሁሉ በቀጣይም በተግባር መመልከቱ የሚበጅ ይሆናል።

ፈቃደኝነቱና ዝግጁነቱ ካለ ካለፉ ስህተቶች መማርና ስህተትን ማረም በራሱ ትልቅ ነገር ነው።

በባዶ ሜዳ የተቀጣጠለ የሕዝብ ጩኸትና አመጽ ለማስነሳት ሳይታክቱ አንዳንድ የግሉን ሚዲያና ጋዜጠኞች እያበረታቱ፤ እያደፋፈሩ፤ መጠቀም፣ ብትታሰሩ እናስፈታለን፤ ብትሰደዱ ጥገኝነት እንሰጣለን፤ ቤተሰብ እንረዳለን .... ወዘተ የሚለው ትላንትም ነበር፤ ዛሬም አንዳንድ ክስተቶችንና አጋጣሚዎችን በተሳሳተ መንገድ መነሻ በማድረግና በተለይም ከቀጣዩ ምርጫ መቃረብ ጋር ተያይዞ ስውር ደባ እንዳለ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ በአደጉና በሰለጠኑና እያደጉ ባሉ በርካታ ሀገራት የፕሬስ ነጻነት ሀገርንና ሕዝብን በሚጠቅም ጎኑ የሚሰሩበት፤ ከጥላቻ ከበሮ ደላቂነትና ጥፋትን ለማየት ከመጓጓት የእብደት ስሜት ተላቀው፤ በስክነና በረጋ መንፈስ የሚሰሩብት፤ የመንግስትንም ሆነ የተቃዋሚውን ፓርቲ ጠንካራና ደካማ ጎን በመለዩት ትምህርት በሚሰጥ መልኩ በተጨባጭ ማስረጃ የሚተቹበትና መፍትሄም የሚያመላክቱበት፤ ብሄራዊ ጥቅምንና ሰላምን በማስቀደም ሁሉም ዜጋ በሕብረትና በአንድነት ለሀገሩ ሰላምና እድገት እንዲቆም የሚያደርጉበት እንጂ ሀገርንና ሕዝብን ወደማያባራ ትርምስና ውድቀት ለማስገባት ሙያቸውን በጥፋት አቅጣጫ አሳልፈው የሚሰሩበት አይደለም።

የፕሬስ ነጻነት አንዱ የዲሞክራሲ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ የአስተሳሰብ ልዩነቶችንና የአመለካከት ጥጎችን ያከብራል፡፡ በእኩልነትም ያስተናግዳል እንጂ ከእኛ የተለየ አስተሳሰብና አመለካከት ያለው ሁሉ ጠላት ነው፤ አድርባይ ነው፤ የሚል የድንቁርና የጨለማ አስተሳሰብን ጭርሱንም አያስተናግድም፡፡ አይቀበልም፡፡ በእኛ አገር አንዳንደ የግል ፕሬሶች ይህንን መርህ ሲያከብሩ ሌሎች ደግሞ የዲሞክራሲንም ሆነ የፕሬስ ነጻነትን ምንነት ከቃል ውጭ በተግባር ሰለማያውቁት ፍጹም ጸረ-ዲሞክራሲና ጸረ-ፕሬስ ነጻነት አቋም ያራምዳሉ፡፡

ለእነሱ የፕሬስ ነጻነት ማለት ሀሜትና የመንደር አሉባልታን እውነት አስመስሎ ማቅረብ፤ ከሕግ በላይ የሆኑ እየመሰላቸውም ያሻቸውን ጽሁፍ እየጻፉ ጽንፈኞችን በመሳሪያነት ማገልገል፤ ሃሰተኛ ውንጀላ ይዞ መቅረብ በእነሱ የወረደ አስተሳሰብ ጀግንነትና ጋዜጠኝነት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ በሕዝቡ ስሜትና ችግር እየነገዱ ርዕስ እያስጮሁ ሆድ እያስባሱ በአቋራጭ የድህነት አቧራን በፕሬስ ነጻነት ስም ከላያቸው ላይ ያራገፉ ስለሚመስላቸው፤ ዛሬም በዚህ አቋማቸው የገፉበት ይመስላል፡፡

በአንዳንዶችም ዘንድ ይህንን ስር የሰደደ ችግር በለዘብተኝነት የመመልከት አዝማሚያ ይታያል፡፡ ምን ያመጣሉ የትስ ይደርሳሉ በሚል ግምትና አባባል ተገቢ መልስ ያለመስጠት ችግር ሕዝቡን የተምታታ ውዥንብርና ያለመረጋጋት ውስጥ እንደሚከተው ስነ ልቡናውንም የማደፍረስ ጫና እንዳለው መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን የላቀ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት በተዛባ መንገድ እየተረጎሙት፣ ለጥፋት ድግስ ተላላኪ በመሆን በመሳሪያነትና በቅጥረኛነት የተሰለፉት ወገኖች፣ የሀገርንና የሕዝብን ታላቅነት፣ ሰላምና መረጋጋት፣ እድገትና ልማት፣ የሀሳብ ልዩነቶች ማክበርን፣ ተቻችሎናተከባብሮ፣ ልዩነትን ጠብቆ በሰላም መኖርን ደግመው ደጋግመው ሊያጠኑት ይገባል፡፡ ሰላምን ለማደፍረስ እየተራወጡ በውዥንብርና ግርግር ፈጠራ ነግጄ አተርፋለሁ፣ እከብራለሁ ብሎ ማሰብ የሕግና የሞራል ተጠያቂነት እንደሚያስከትል አስቀድሞ መገንዘብ ተገቢ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ለሃገርና ወገን ጥቅምና ክብር መረጋገጥ በኃላፊነት ስሜት ሙያዊና የዜግነት ግዴታን መወጣት ላይ እናተኩር የሚለው መልዕክቴ ነው።